# ኢ.ምንት ሰንኮችን ሲመዘምዝ የሚኖር የራሱን ዘርፈ ብዙ ጉድፍ ሳይነቀስ ያሽልባል

ከእውነት መዘገቡ

ሽምግልና የእድሜ ባጸጋነት ፤ ለሀገር መኩሪያ ፤ የታሪክ ማጣቀሻ ፤ ለአካባቢም ሆነ ለመንደረተኛ ነዋሪ ሁሉ ምክር ለጋሽ እና ችግር ሲፈጠር ያስታራቂ ያልህ ተብሎ ከአምላክ በታች የሚኬድበት የአንድ ህብረተሰብ መመኪያ ዋርካ ነዉ። < ባይበሉ ባይጠጡ ባይመች ትራሱ ደስ ይል የለም ወይ አባት ሽማግሌው ሲገኝ ከሰፈር ከቤቱ> ተብሎ ተቀኝቶላቸው የለ።

ከዝህ ባሻገር አባቶቻችን ለቀጣይ ትውልድ መልካሙን ፡ መከባበሩን፡ አገር መውደድን፤ ከራስ በፊት ለሀገር እና ለወገን ማሰቡ የሚያስገኘውን ክብር፤ ቀራጥነትን ፤ መተሳሰብን ፤ መፋቀርን እንድያው ምኑ ቅጡ ሁሉን ለሃገርና ለማንነት የሚበጅውን ሁሉ እያስተማሩን አልፈዋል። አሁንም ቢሆን እያስተማሩን ያሉ አበው አባቶቻችን እንዳሉ ግልጽ ነዉ።

የእድሜው ጋፋ እና የእውቀቱ ቁዋት ሳይርቃቸው ከላይ የተጠቀሰው የአባቶቻችን ችሮት የራቃቸው ጥቂት ወንድሞች እንዳሉ እና መልካሙንም ሆነ ኢ.ምንት የሆኑ ሰንኮችን በመኮነን ብቻ መኖር እንደባለዛር የተቆራኛቸው ፤ የተናወጣቸው በተለይ ባህሉ እና ቅጡ በጠፋበት፤ በተወናጀበበት የውጭ ምድር ሆነው በአንዳድ የዘመኑ ድህረ ገጾች በሚጽፉት ጽሁፍ እና መያዥያ በሌለው አስተሳሰባቸው እኛ የአዲሱ ትውልድ ውጤቶች እየመዝናችው ስለሆነ የኢትዮጵያ አምላክ ቅንነቱን እና ለነገው ትውልድ የማሰብ አእምሮ እንዲለግሳቸው እንጸልያለን።

<ሁሉን ቢናገሩ ሆድ ባዶ ይቀራል> እንዲሉ መላው የሀገሬ ሕዝብ እውነታውን ስለሚያውቀው መደጋገሙ < ጆሮ ማቆርፈድ > ይሆናልና ወደ ዋናው ቁም ነገር ቀልባችን ጎራ እናርግ። ህብረተሰቡ የትየለሌ ሪከርድ ሰብሮ ያመለጣችው ወንድሞቻችን በውጭ ያለው ቅን አሳቢ ወገን <ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ > እንዲሉ በንቀት መኮነናቸው አንገብቦን ይህን ጽሁፍ ለመከተብ ተገደናል።

ይህን ልንል የቻልነው በውጭ ሃገር ያሉ በእጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ወንድም መሰል ፤ ነገር እና እሳት በወገን ላይ ለመጫር ትላንትም ያልታከቱ ዛሬም እነሱ የስልጣኑን እርካብ እስካልጨበጡ ድረስ ኢትዮጵያ እና ሕዝብዋ ኖሩ አልኖሩ ደንታ የሌላቸው ስላሉ ከእነዚህ መሰል ሳጥናኤሎች እና ዳያቢሎሳዊው አስተሳሰባቸው እንድንርቅ በማሰብ ነው።

እነዚህ < የእናት ወጪት ሰባሪውች> ትላንት የምየ ኢትዮጵያን አንጡራ ሀብትን ጠራርገው የሸሹ ፤ ለምየ ኢትዮጵያ ይሄነው የሚባል ቅንጣት ስራ ያልሰሩ ፣ < ጅብ ከማያውቁት ሃገር ሄዶ ቆርበት አንጥፉልኝ > እንዲሉ < መሳይ ቅቤ አንሻአቾች> ሲዛላብዱ ማየቱ የተሸከሙትን እዳ ፤ የወገን እደራ ባለመክፈላቸው እንዲዘላብዱ ምክንያት መሆኑ ከሚጽፉት  አንቶ ፈንቶ ጽሁፋቸው የሚታይ ነው።

እስኪ ትንሽ ከጻፉት ሕግን እና ስረአትን ያልተበቀ ንግግሮች እና ጽሁፎች ትንሽ ለጀሮ ቢሰቀጥጥም ሕዝብ ፍርድን ኢንዲስጥ እንጠቃቅስላችሁ ፣

< ሕዝባችን በዚህ ተታሎ እንዳይሄድ ብንነግረውም፣ የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል ሆኖበት መሰል 200 የሚድርስ ስደተኛ ሂዶለታል የሚል መረጃ ደርሶናል። ሒሊና-ቢስነት ይሉሐል ይኸ ነው። ለወገን ደንታ-ብስነት ይሉህል ይኸ ነው። ለሆድ ሲሉ ወገንን ማስጠቃት፣ ወገንን አሳልፎ መስጥት ማለት ይኸ ነው። ዛሬ ለሆዱ የተሰለፈለት የዋኅ ሕዝብ ነገ ለሕሊናው ይሰለፍበታል። እንዲያ አልነበር በቅንጅት ጊዘ የተፈጸመው? አሁንም ያ ይደገማል።  >

ተመልከቱ ውድ ወገኖች የንቀታቸው ንቀት ሕዝብን በተራ ስድብ እንዲህ አርጎ በግልጽ መስደብ እንኹኣን ሕዝብን ግለሰብን ባልውለበት ማንሳት እና ማጥላላት ቢኢትዮጵያም ሆነ በአልም ሕጎች < Article on Defamation>የምያስቀጣ እና ሕዝብን የምያስቆጣ መሆኑን አለማውቃችው የሚያሳዝን ነው ፣

ብዙወቹ ለሕዝባቸው ካላቸው ርህርሄ ቢሴነት የተነሳ የሀገርቤቱን መስፈርተ ትምህርት ስለአላሙአሉ በስታሊናዊ ቀነኖ ችሎታቸው ባአመዛኙ ክህኖት ስላላቸው ተመርጠው ለትህምርት ወደ ስታሊን ተቓም ያተላኩ አፍቅሮተ ኢትዮጵያ ፤ ቴውድሮስ ፤ ዮሐንስ፤ ሚኒሊክ፤አባጂፋር፤አሊ ሚራ፤አባ ጠና እና መሰሎቹ ሳይሆን አፍቅሮተ በለው ፣ ግደለው፣ ረብሸው ፤ ናቀው፤አናቁረው፤ዝረፈው፤ቅናበት፣ አታስራው፤መልካም አታስብ በለው እና ሌሎች ሰይጣናዊ ኮርሶችን ወስደው የተካኑ በመሆናቸው ጥሩ ሲሰራ አበጃችው ይላሉ ማለት የማይታሰብ ነው። ሌላው በውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊ እነሱን እና መሰሎቻቸውን በቃችሁን ስላለ ብቻ እንዲህ ሲሉ መኮነናችው እና ማጣጣላቸው ኢትዮጵያዊው የነሱ ገባሪ እንድሁም ታዛዣዥችው ሆኖ እንዲቀር ምንኛ እንደሚያውጠነጥኑ በማሳየት እንዲህ ሲሉ በድፍረት ተናግረዋል ፣

<የሚገርመው ግን የዋሁ ሰደተኛ ማትረፉን እንጂ መዘረፉን ወይም እራሱ መጠቀሚያ መሆኑን አለመገንዘቡ ነው። ንብረት ኢትዮጵያ ውስጥ ማፍሰስ የቻለ ስደተኛ፣ ለምን ውጭ አገር እንደሚኖር በመጀመሪያ ደረጃ አይገባኝም። የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አንተም አብረህ ዝረፍ የሚባለውን አባባል ተከትሎ ተባብሮ ሊመዘበራት ከሆነ፣ ያው እሱም ሌባ ነው።:>

የጻፉት ጽሁፍ ሁሉም ስረአትን ያልተከተለ ፤ ተተኪውን ትውልድ መልካም ቃል ከማስተማር ይልቅ ፈረንጅ ሀገር ምናምኑን ፋት እና ቅምስ እያደረጉ በሚሰነጥሩት ልቅ በሆኑ ቃላት ስድባቸውን በማዥጎድጎድ ወጣቱን ፤ መላውን ሕዝብ እንደ አጋር ሕዝብ ባለመቁጠር ብያብጠለጥሉትም ለእነዚህ መሰሉ ከራሳቸውም ሆነ ከመንፈሳቸው ጋር የተጣሉትን ወንድሞች ወደ ጎን በመተው መላው ወገን በህልህ ተነስቶ ሀገሩን የማልማቱን ስራ አጽንሆት ሰጥቶ ሊንቀሳቀስበት ይገባል።

ሃገራችን ኢትዮጵያ የብሔር ብሄረሰቦች ግማጅ እና አንዱ ብሔር ከሌላው ብሔር የተሳሰረባት ምድር መሆኑዋን ። እኛ ልጆቿዋ የብሔር ብሔረሰቦችዋ እጹብ ድንቅ ውጤቶች መሆናችን መናገር ለቀባሪ እንደማርዳት ነው:: ይሂን ቅምረ ውጤት ይበጅ የምንለውን እንዲሁም  ታላቁዋን ባለውለታ ሀገራችንን ፤ ያስተማረን እና አይዞአችሁ ብሎ ያሳደጋንን ወገናችንን መደጋፉችን።

< መልካም ያሰበ መልካም መከር ይሰበሰባል > የሚለውን የአብ እና የአበው ቃልን ይዘን በመነሳት ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲሁም የስራችን ውጤት አምሮ እና ሰምሮ መታየቱ ያስቀናቸው እና እንደ እግር እሳት ያንገበገባቸው ወንድሞቻችን ሳይቀር እኛን መስለው ወገንን በመርዳቱ ስራ እና ወደ መልካሙ ማሳ ገብተው በጉልጉዋሎው እንኩዋን እንድያግዙን እንጋብዛቸዋለን።

ከሁሉ በፊት በእህት ኢትዮጵያ በቀል ልማት ማህበራት ላይ በታዳሚነት በተገኘሁበት ወቅት ኢትዮጵያውያዋ ታላቅ ምሁር የሕክምና ዶክተር ከላይ የተጠቀሱትን ሃሳበ ጎባጣ ወንድሞቻችንን አመለካከት ቀና እና ይዌግሽ ዘንድ < ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ አካባቢውች የሚሰራ የውሃ ፡ የህንጻ፤ የመንገድ ፡ የጤና ጣቢያ ሆነ የመሰረተ ልማት ኢሕአድግ ኢሕአድግ፤ቅንጂት ቅንጅት፤ህብረት ህብረት የማይል እና የኢትዮጵያውያን መጪ ትውልድ ሃብት ነው> በማለት እቅጩን በማብሰር የታዳሚውን ቀልብ የሳበ ታላቅ ጥቅስ ተናግረዋል። በሃገራችን ተቓማት የተፈጠሩ ሙሁራን ምልሁ መሆናቸውን የምያስገነዝብ እና ትልቅ ትምህርት በሁላችን ህሊና የሚጭር መሆኑን ይገነዘቦዋል።

ለነዝህ ወንድም መሰል ሁሉን ሂደት የመኮነን አባዜ የተጠናወታቸውን ኢምንቶች ልንነግራችው የሚገባው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እንደባአንዴራችን አሸብራቂ መታወቅያችን መሆናችውን ነው። አማራ ፤ ትግሬ ፤ ኦሮሞ፤ አፋር፤ ሱማሌ፤ወላይታ፤ሲዳማ፤ጉራጌ፤ ሀረሬ፤ጋምቤላ፤ገሚራ፤ሃድያ፤ አገው ሌሎችም ከሰማኒያ በላይ የሆኑት ብሔሮች ባህላቸው እና ቓንቓቸው ተካቶ በዘርፈ ብዙው የሶስት ሺህ አመት ታሪካችን የአንድ አባት እና እናት ልጆች ስም የተለያየ መጠርያ እንዳላቸው ሁሉ በታሪክ አጋጣሚ የተለያየ መጠሪያ ተላበሱ እንጂ ከአንድ ስረወ ግንድ ዘር ተሰበው የወጡ ወንድም እና እህቶች መሆናችው ልያውቁት ይገባል።

እንግዲህ ከሀገር ውጤት የታሪክ ጸሀፊወች የነ ፕሮፌሰር ላጺሶ ጌዲልቦን ፤ የነ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያን ፤የነ ዶ/ር ብሕሩ ዘውዴን እንዲሁም የሌሎች ኢትዮጵያዉያን የታሪክ ከታቢውች እና አዋቂ የሀገር ቤት ሽማግሌወችን እምቅ የታሪክ አዋቂ አባቶቻችን ተምህሮት ሊያዳምጡ ይገባል። ከውጮቹ ደግሞ የነፕሮፌሰር ክላውዲዮ ሳምነርን እና የነፕሮፈስር ፓንክረስትን የሌሎችን መድበለ ታሪክ ጽሁፎችን በማንበብ ተሳስቦ እና ተከባብሮ የመኖር ታሪካችንን እንዲማሩ እንነግራቸዋልን።

እንግዲህ የእነዚህ ብሔር ብሔራሳቦች ወንድም የሆነው አማራው በተለያዮ የኢትዮጵያ ክፍሎች እና ክልሎች ሰፍሮ የሚገኝ ሲሆን ከቅድመ ሀያቶቹ የተሰጠውን ማንነት በማተቡ አስሮ የራሱ ሰፋ ያለ ክልል ተሰጥቶት ስሜናዊውንና ማእከላዊ ኢትዮጵያን ተጋርቶ በመኖር ላይ ይገኛል።

በለፉቱ ዘመናት ለአማራው ሕዝብ ምን ተደረገለት ቢባል በስሙ ተነገደ እንጂ ለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አካል ከመራራ ስሙ ፣ ድህነቱ እና የጠርነት ሰለባ ከመሆኑ ባሻገር ምንም የተሰፍረለት መቁንን ለአመል ያህል እንኳን የለም።

በጣም የሚከነክነው ና የምያሳዝነው የአማራው እፍኝ የማይሞሉ መሰል ውንድም ተወላጆች በአለፈው የመንግስት ዘመናት ስልጣኑን ጨብጠው በነበረበት ጊዜ ወገናቸው እትብቱ ከተቀበረበት ሰፈር በተለያየ ኢምንት ምክንያት እንዲፈናቀል ፤ እሱነቱ እንዲራቆት ፤  አንጡራ ሃብቱን እንዲያጣ ፤ ወገኑን ዞር ብሎ እንዳያይ ፤ ያፈራው ንብረት በመውረስ ፤ የመማር እድሉ ለነሱ እና በነሱ ዙሪያ ላሉ ቤተሰቦቻችው በማድረግ እንዲሁም በመንደር ከፋፍለው ወገን ከወገኑ እርስ በርሱ በደመኝነት እንዲታይ ያደርጉ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ሸሽተው ከተቀመጡበት ጉሽግሻ ውጭ ሀገር እነዚሁ ያለፈው ክፉ ስራቸው አልበቃ ብሎ በውጭ ያለውን አማራ ወገን ከመኮነን አልፈው አማራውን ጎንደር ፤ ሸዋ ፤ ጎጃም ፤ ውሎ እና በሌላው የኢትዮጵያ ምድር ቢወልድም ብሔሩ ሌላ ነው እያሉ መለጣጥፋቸው እንኳን የሌላ ዜጋ አላደርጉት እንጂ ይሄም ባልከፋ። ይባስ ብልው አማራ ወገናችንን እንደሌላው ብሔር ብሔረስብ ተድራጅተን ክድህነት፤ ያሳረፋበን ጠባሳ እንዲያገግም ፤ እንዲያጠግግ፤ እድንፋቀር፤ እድንዋዋደድ፤እንድንገናኝ፤ የተካነውን ኪናዊ ጥበባችንን እንድንለዋውጥ እና እንድንረዳዳ እያደረግን ያለው ሰናይ ስራ እንዲከሽፍ ብያሸርቡም በልጅ አዋቂ ጥበበኛ ልጆቹ እየከሸፈ መሆኑ ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ ሁላችንንንም አሰንዮናል።

ሰሞኑን አንድነት ኢትዮጵያ በሚል ሰናይ አላማ ወጣት የአገራችን ውብ ውጤቶች ገና፤ ገበጣ፤ ባሕላዊ ትግል እና መሰል ውብ ባሕላዊ ስፖርታዊ ጭዋታወችን ለማጣጣም ባይታደሉም ባሉበት ሀገር ታላቅዋ ብሪታንያ ተቀባይነት ባገኙ የተለያየ ስፖርቶች ወገንን ለማገናኝት መሞክራቸው አይዞኣችሁ ፤እደጉ ተመደጉ ፤ ለሀገራችሁ ምድር ያብቃችሁ መባል ሲጋባ በእነዝህ ታዳጊ ወጣቶች ላይ ለኛ እና ያለኛ በሚሉት ከመወረፋችው አልፎ አገር አልፎ በተመሰረተ ድህረ ገጽ እንደሚከተለው ሰራቸው እንዳይሰምር የስም ማጥፋት ስራ ተፈጽሞባቸዋል ፣

<  ወጣትነት የእሳት ዘመን ነው። ወጣቱ ስደተኛ የእግር ኳስ ጨዋታ፣ የኢትዮጵያ ዘፈንና ጭፈራ ይወዳል። ባለሥልጣኖች ዓላማቸውን ለማሳካት ሲሉ የአጎት የአክስታቸውን ልጆች በስደተኛ ስም በገፍ ወደ ሎንደን አግዘዋቸዋል። ሥራ ፈጥረውለት መሆኑ ነው። ታዲይ እነዚህ አስመሳዮች ከዕውነተኛ ስደተኞች መሐል በጓደኝነት መልክ፣ በኳሱ ሜዳ፣ በጫቱ በርጫ፣ በየጭፈራው ክበብ ተሰግስገው ሰይጣናዊ  ተግባራቸውን በሰፊው ተያይዘውታል። ልብ ማኮላሸቱን ቀጥለውበታል። እንግዲህ አንዱና ዋነኛው በሎንደን የስፖርት ፍቅር የሳባቸውን ወጣቶች አድብቶ የሚያጠምድ ፣ ________በመሪነት ተሰማርቷል። እያንዳንዱ የዚህ ቡድን አባል ማን ማን እንደሆነ ያውቃል።

አላሙዲም ብቅ ሲል ስኳር እንደሚያቅማቸው እናውቃለን። ልጆቹ በተለያዩ ድለላ እንደተያዙም ሳይታለም የተፈታ ሐቅ ነው።>

እንዲወረፉ ተሞክሩኣል ። ነገር ግን ይህን ሁሉ አልፈው አኩሪ ስራ መስራታቸው በመላው ኢትዮጵያዊ ዘንድ ተውድሶላቸዋል።

በቅንጅት እና በተለያየ የተቃዋሚ ቡድን ስም በውጭ ሀገር አውራጎዳናውች ወገንን እያንከራተቱ ኢትዮጵያዊነት ሞራሉ እና ማንነቱ  ጥያቄ ውስጥ እንዲጋባ መሞከራቸው አልበቃ ብሎ ትላንት እንደግሪኮቹ ጨፍጨፊ መሪውች ፒሲስትራትስ/ Pisistrasus/ ፤ሲያክስ /Syacus/፥ዲንይሶስ /Dinysos/ ፤ ለአለም ጥቁር ጠባሳ ጥልው እንዳለፉት ጨካኞች ስታሊን /Stalin/ እና መስሎቹ  ሕዝብን እየጨፈጨፉ በወይን ሲራጩ ሲያቀነቅኑ እንደነበሩት ለኛውቹ  ግዳዮቹ መላኩ ተፈራ ፤ መንግስቱ ሃይለማርያም እና ሌሎችም ሲያቀነቅኑ የነበሩ የገዳዮቹ ሊቀመኩዋሶች በአሜሪካ እና በአውሮፓ የተረፈ ወጣት የለም ብለው ስለሰባዊ መብት ሲዘምሩ ላየ <ለማያውቃችሁ ታጠኑ እኛስ እናውቃችዋለን> ብለን እንደነሱ ሃሳብ ሳይሆን አላማችውን ፉርሽ አድርገን ውደ ልማቱ እና የወገናችንን እንባ ወደመጥረጉ ፤ አበጀችሁ ወደሚያስብል ስራ ልናቀና ይገባል።

ወገን ያለፈው ስህተት ቀጭቶት ፤ በአስመሳይ ወንድሞች መኮነኑ አንገብግቦት ላልሆነ አላማ ያዋጣው ገንዘብ የተቃዋሚ ቡድን መሪ ነን ባዮች በአውሮፓ ታላላቅ / Five star hotels/ ሆቴሎች መዝናኛ እና ዘመናዊ መኪና መግዣ እንዲሁም አያፍሩም እና አገርቤት ድረስ ቪላ ቤት የኛ መንግስት ይመጣል በሚለ ቀቢጸ ተስፋ እየገነቡበት መሆኑ ከንክኖት እያጋለጣቸው መሆኑ ሊታወቅ እና <ሆድ ስያውቅ ደሮ ማታ> እያላቸው መሆኑን ሊገነዘቡት ይጋባል።

ሰሞኑን በሃገራችን  ኢትዮጵያ የአማራ ልማት ማህበር ባዘጋጀው የገንዘብ ማሰባሰብያ ፕሮግራም ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢልዮን በላይ መዋጣቱ አሰንዮት በውጭ ያለው የአማራ ተወላጅ እና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ወገን ድጋፉን ሊቸር ሲንቀሳቀስ እኛ ኪስ ይጋባ ያነበረው ገንዘብ ለወገን እና ለህገር ልማት ዋለ ብለው ያንፈረፈራችው መዝባሪውች ወገንን በተራ ስድብ መሳደብ ስራየ ብለው ይዘውታል። ከዝያም አልፈው ለነሱ በቆሙ እና የጥላቻ ውዝንብር ነኸ ድህረ ጋጻችው የወገንን ርብርብ ፤ ቀና መተሳሰር እና መግባባት አስቀንቶአቸው መርዛቸውን በቅናት መንፈስ < ድያብሎስ የአዳምና ሔዋን በገነት መኖር አስቀንቶት ለሰህተት ዳርጎ ከገነት እና እስከሞት> እንዳበቅን ተምሳሎት ሆኖ እነዝህ በጣት የሚቆጠሩ የሰው ድያቢሎሶች የውጩን ኢትዮጵያዊ ወገን ከማተራመስ አልተቆጠቡም። ከዚህ በፊት http//www.nazret.com ወይም <Crisis in Diaspora and the role of websites > የሚለውን በቀጥታ <Google> ገብቶ በመጫን እንዚህ ደህረ ገጾች እና ጽሃፊውቻቸው እንዲማሩ የተደራገውን ጥረት ያንቡ።

እነዝህ መሰሎቹ ጥቂት የሰው ሳጥናኤሎች ለሩቁ ወገናቸው እና ወንድሞቻቸው ሊያስቡ ይቅርና ውጭ ላሉ ቅርብ ወንድሞቻቸው የማይተኙ ፡ ከኛ በላይ ላሳር የሚሉ እና የወገንን ገንዘብ ለስሙ በአቃቃሙት አሸሸው ገዳሜ ማያቸው እና የኮሚኒቲ መዝናኛቸው የመዘበሩትን ሲከፋፈሉ እና ሲቃራመቱ ላየ የምያስደምም ነው። የሚያስገርመው < ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል > እንዲሉ የመኖሪያ ፈቃድ እናሰጣችዋለን በሚል የቀቢጸ ተስፋ የተመዘበረው የውጭ ወገን የትየለሌ ከመሆኑ ሌላ የማስፈራራት እና የማስጠንቀቅያ ቃላት እንደሚጽፋት ያጃፈተ ጽሁፋቸው የደረሰው ብዙ ነው።

ይህን ተንተርሶ በአሜሪካ ፤ በአውሮፓ ፤ በኢሲያ እና በመላው አለም ያለው ኢትዮጵያዊ አገር ውስጥ ካሉት እውቅና ካገኙ ታላላቅ እሰየው የሚያሰኝ ስራ እየሰሩ ካሉ የልማት ማህበራት ጋር አጋር በመሆን ግልጽነት፤ ተጠያቂነት ፤ ተጨባጭ እና የሚታይ ስራ ለመስራት እያደረጉት ያለው ሰናይ እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ መሞከሩ በተጻጻሪነት ላሉ ቡድኖች ሆነ ግለሰቦች የሽንፈት ጽዋ እያጋታቸው ያለ እና ለመውደቅ እይተነገታገቱ ያሉ መሆኑን ከሚጽፋት እንተፈንቶ እየታየ መምጣቱ ግልጽ እየሆነ መጥትዋል። ይህን እሰየው የሚያሰኝ እምርታ ወደ ፖለቲካ ማእቀፍ ውስጥ አካቶ ለማየት መሞከሩ ፤ በምን መልክ አገርን እና ወገንን እንዴት መርዳት እንደሚቻል አማራጭ ሳያቀርቡ በቅናት መንፈስ ወገን ባገሩ ልማት በቁጭት ሆ ብሎ ለምን ተነሳ በማለት ቡራ ከረዩ ማለታቸው የሚያስተዛዝብ ነው ።

ስለዚህ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን መሰል ሁሉን በመኮነን የሚኖሩ ወንድሞች ለወገናቸው መልካሙን የማይመኙ ራህይ የሌላቸው / those who are always pessimistic / ጆሮ ሳንሰጥ ፤ ቀና የሆነውን ሁሉን ኢትዮጵያዊ ያንቀሳቀሰ ቅን ስራ ሊያጨናግፉ የሚፍጨረጨሩትን እንዲሁም ወገንህን የምትረዳው ገንዘብ ወደእኛ ኮሮጃ እና ኪስ ካልገባ የሚሉትን ስግብግቦች እና የቀን ጂቦች እየተዋጋን ወገናችንን በሃሳብ ፤ በቁሳቁስ እና በቻለነው ሁሉ የመርዳቱን ስራ በማሳለጥ እነዝህን መሰሎችን ጥቂት የወንድም አሚካላውች ልናሳፍር እና ልናስተምር ይገባል።

ሌላው አማራ ፤ ኦሮሞ ፤ ጉራጌ፤ ትግራይ ፤ቤንሻጉል፤ ጋምቤላ ፤ ሐረሬ እና ሌሎች አካባቢወች ለሙ ማለት የነገዋ ኢትዮጵያ ለማች ማለት ከመሆኑ ባሻገር መንግስት እንደመንግስትነት የሚሰራቸው ስራ እንዳለ ሆኖ የነገዋን ኢትዮጵያ ለመጭው ትውልድ አስተካክሎ የማስረከቡ አላፊነት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከፖለቲካ ፍጭቱ ውጭ ሆኖ ሊገፋበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

ከዝህ ባሻገር ኢትዮጵያ ያሉት ንብረቶች ፤ አንጡራ ሀብቶች ፤ ቅርሶች እንድሁም የትውልድ አሻራውች ሆነ በውጭ ያሉ መሰል አሴቶች፤ኢምባሲወች ፤ ከመሬት በላይ ያሉ ሆነ ከመሬት በታች ተቀብረው ሃገራችን መሉስን ብለው ጩህታቸውን እያሰሙ ያሉ ቅሬተ አካሎች እንዲመለሱ መጣር የሁላችን

አላፊነት ሆኖ እነዝህ ንብረቶች የኢትዮጵያን እና የመጪው ትውልድ ንበረቶች እንጂ ያለው ሆነ ያለፋት መንግስታት ሃብት አለመሆናችው ታሪክ እያሳየን እና በተጨባጭ እያየናው ስለሆነ አሁን ያለውን ትውልድ ሊያስነሳ እና ሊያስመሰግን የሚያስችል ቅርስ ትቶ ማለፋ ሊታሰብበት እና የተቻለንን ማድረግ እንደሚጋባ ልናስብበት ይጋባል።

በአጠቃላይ እኛ ኢትዮጵያውያን የውጩን አለም እውንታ አገራችን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሳናነጻጽር በፖለቲካ መስተካከል/ Political correctness / መርህ ላይ ብቻ አተኮሮ ለመንቀሳቀስ መሞከሩ የማያስኬደን መሆኑን ልንገነዘብ ግድ ይለናል። ከዝህ አልፈን ግን ዛሬን አስረግጠን ለነገው ትውልድ በማሰብ የመሰራቱን ትብእል በመታጠቅ በጋራ የኢኮኖሚ ፡ የማህበራዊ እና መሰል የልማት ግንባታወች ተግባር ላይ በመረባረብ መከወን ያለብንን ስራወች ከወዲሁ አስበንበት ልንቀሳቀስ የግድ የሚለን ይሆናል።

ከእውነት መዝገቡ / ከታላቅዋ የእንግሊዝ ምድር/

---

1- Crisis in Diaspora and the role of websites